ዲፓርትምንት ኦፍ ሀውሲንግ ኤንድ ኮሚዩኒቲ ደቨሎፐመንት (ዲ.ኤች.ሲ.ዲ)

ኢመርጀንሲ አሲስታንስ (ኢ.ኤ) ፕሮግራም

የልጅ እንክብካቤ መመሪያዎች – 2015

1. ማረጋገጫ ለማግኘት፣ ልጅ ተንከባካቢዎች በእነዚህ መመሪያዎች የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

2. የልጅ እንክብካቤ ለማግኘት የሚፈልጉ ቤተሰቦች ቢያንስ ከሁለት የስራ ቀናት በፊት ማረጋገጫ መጠየቅ አለባቸው። በተጠጋጋ መጠለያ ለሚኖሩ ቤተሰቦች፣ የመጠለያው ሰራተኛ ፈቃድ መጠየቅ አለበት። ሆቴል ውስጥ ለሚኖሩ ቤተሰቦች፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ ፈቃድ መጠየቅ አለበት። የሆቴል ሰራተኞች የመገኛ አድራሻ ስለሚኖራቸው የቤተሰቦችን ቅፆች ወደ ዲ.ኤች.ሲ.ዲ ይልካሉ። ለልጅ እንክብካቤ ቢያንስ ከሁለት ቀናት በፊት ጠይቀው ከነበረና ምንም ምላሽ ካላገኙ፣ ጥያቄዎ ተቀባይነት አግኝቷል።

3. ልጅ ተንከባካቢዎች በአንድ ጊዜ ከስድስት (6) ልጆች በላይ አገልግሎት መስጠት አይችሉም፣ የተንከባካቢውን(ዋን) ልጆች ጨምሮ (ያላቸው ከሆነ)። በሆቴሎች ውስጥ፣ ልጅ ተንከባካቢዎች የራሳቸውን ልጅ ጨምሮ በአንድ ጊዜ ከአንድ ቤተሰብ ልጆች በላይ ሊንከባከቡ አይችሉም። ከሁለት በላይ የሚሆኑ ከሁለት ዓመት በታች የሚገኙ ህፃናት ከተመሳሳይ ተንከባካቢ በአንድ ጊዜ አገልግሎት ሊያገኙ አይችሉም። ብዛታቸው ከሁለት በላይ የሆኑ ከሁለት ዓመት በላይ የሆናቸው ህፃናት ከሁለት አመት በታች የሆነ(ኑ) ሌላ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ህፃን በመንከባከብ ላይ ከሚገኙ ተንከባካቢ አገልግሎት ሊያገኙ አይችሉም።

4. ህፃን ተንከባካቢዎች ቢያንስ 16 ዓመት ሊሆናቸው ይገባል። ታላቅ እህት ወይም ወንድም ከሆኑ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ከሆኑ ግን ቢያንስ 14 ዓመት ከሆናቸው በቂ ነው። ከ14 እስከ 16 ዓመት ውስጥ የሚገኙ ልጆች ለታናናሽ የቤተሰብ አባላት በተመደበው ክፍል ውስጥ ብቻ ወይም ህፃኑን(ኗን) ከትራንስፖርት ወደ ቤት (ወደ ሆቴል) ወይም ከቤት (ከሆቴል) ወደ ትራንስፖርት በሚያደርሱበት ጊዜ ብቻ እንክብካቤ ሊያደርጉ ይችላሉ።

5. ልጅ ተንከባካቢዎች በአንድ መጠለያ ወይም ሆቴል ውስጥ የሚኖሩ የኢ.ኤ የቤተሰብ አባል መሆን አለባቸው። በቤተሰብ መጠለያዎች ለተቀመጡ የኢ.ኤ ቤተሰቦች ብቻ የመጠለያ ሰራተኛ የሌሎች ተንከባካቢዎችን ጉዳይ በተናጥል በማየት ሊያፀድቅ ይችላል። በተበታተኑ ጣቢያዎች ለሚገኙ የኢ.ኤ ቤተሰቦች፣ ይህ ማለት ተንከባካቢው(ዋ) የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት የሚያገኙት የኢ.ኤ ቤተሰብ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መጠለያ አቅራቢ ቁጥጥር በሚደረግበት የመጠለያ ፕሮግራም ተሳታፊ መሆን አለባቸው አለበለዚያም በመጠለያው ሰራተኛ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።

6. በእነዚህ መመሪያዎች መሰረት የሚደረጉ ማናቸውም የልጅ እንክብካቤ አገልግሎቶች ያለምንም ክፍያ መደረግ አለባቸው።

7. በዚህ ስምምነት መሰረት የሚደረጉ የልጅ እንክብካቤዎች በመጠለያው በተከለሉ ሆነው የተንከባካቢውን(ዋን) ክፍልና የእንክብካቤ አገልግሎቱን የሚቀበለው የኢ.ኤ ቤተሰብ ክፍል ሊያጠቃልል በሚችል ቅጥር ግቢ ውስጥ (የተበታተኑ ጣቢያዎች መጠለያ ክፍሎችን ወይም ሆቴሎችን ጨምሮ)፣ ወይም ሌላ በመጠለያው የቀረበ ቦታ ወይም በመጠለያው ለልጅ እንክብካቤ በተከለሉ የጋራ አካባቢዎች ብቻ መሆን አለበት። ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ተንከባካቢዎች እንዲንከባከቧቸው የተሰጧቸውን ልጆች በግልፅ ፈቃድ ሳያገኙ ከመጠለያቸው ወይም ከሆቴላቸው ይዘው መውጣት አይችሉም።

8. በመጠለያው ወይም በዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ የታመነበት በቂ የጎልማሳ ሰው ቁጥጥር ከሌለ በስተቀር የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት በሚሰጥበት ክፍል ውስጥ ሌሎች ልጆች ሊገኙ አይችሉም።

9. በመጠለያ ውስጥ የልጅ እንክብካቤ የሚሰጡ ተንከባካቢዎች የልጅ እንክብካቤ የሚሰጡበት ማንኛውም ክፍል ያልተቆለፈ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

10. ልጅ ተንከባካቢዎች በማንኛውም ጊዜ አግባብነት ያላቸውን ሁሉንም የኢ.ኤ ድንጋጌዎች እና የመጠለያ ህጎች ማክበር አለባቸው።

11. እነዚህን መመሪያዎች መሰረት ያደረገ ስምምነት የሚሰጠው በልጆች የኢ.ኤ ቤተሰብ («በወላጅ») እና በተንከባካቢው ከተፈረመ በኋላ የመጠለያ ምድብ ከሆነ ለመጠለያ ሰራተኛ ወይም የሆቴል ምድብ ከሆነ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛ የቀረበ የተለመደውን ቅፅ የኢ.ኤ የልጅ እንክብካቤ ውሎችን የያዘ የልጅ እንክብካቤ ስምምነት ተሞልቶ ከፀደቀ በኋላ ብቻ ነው። በተጨማሪም፣ ተንከባካቢውና ወላጅ የተለመደውን ቅፅ የኢ.ኤ ህፃን መረጃ ገፅ የልጅ እንክብካቤው ከመጀመሩ ከጥቂት ጊዜ በፊት በተገቢው ጊዜ የየራሳቸውን ክፍል ከሞሉ በኋላ የልጅ እንክብካቤው ከመጀመሩ በፊት (የላይኛው ክፍል ብቻ) እና ከልጅ እንክብካቤው ምደባ በኋላ (የተሟላውን ቅፅ) ቅጅዎችን የመጠለያ ምድብ ከሆኑ ለመጠለያ ሰራተኛ ወይም የሆቴል ምድብ ከሆኑ ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ወይም ለሆቴል ሰራተኛ መስጠት አለባቸው።

12. የዘወትር/ቀጣይነት ያላቸው የልጅ እንክብካቤዎች ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ እና ይህን ቅፅ ለሚጠቀሙ ወላጆች ይሙች ዘንድ ቀደም ብለው ሊፈቀዱ ይችላሉ። ይህም ቢሆን ማንኛውም የልጅ እንክብካቤ ተግባር ለመጠለያው ወይም ለሆቴሉ ይፋ መደረግ አለበት።

13. ምንም እንኳ የልጅ እንክብካቤ መመሪያዎች አስፈላጊ በሚሆኑበት ልክ የሚተገበሩ ቢሆንም፣ 14 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በሆናቸው ልጆች ለሚደረግ ራስን በራስ መንከባከብ የልጅ እንክብካቤ ስምምነቱን መሙላት ወይም የልጅ እንክብካቤ መረጃ መሙላት አስፈላጊ አይደለም።

14. ታናናሾቹን የቤተሰብ አባላት በተመደበ ክፍል ውስጥ ወይም ከጣቢያው ውጪ ወደሆነ ቦታ በሚያደርስ ወይም ከውጪ ወደ ጣቢያው ከሚመልስ ትራንስፖርት ውስጥ እንክብካቤ የሚያደርግ እድሜው በ14 እና በ16 ዓመት መካከል ያለ ልጅ ልክ እንደሌሎች የልጅ እንክብካቤዎች ሁሉ የለጆ እንክብካቤ ስምምነት መፈረም አለበት።